# ለሕዝባዊ ትግል ማዕበል ብቃት-ያለው ኅብረተሰብ፣ ብቃት-አልባ አመራር፤

ዛሬ በአገራችን እየተከሰተ ያለው ሁኔታ እዛው በዛው በጣም ግልፅም በጣም ውስብስብም ነው:: በአንድ በኩል በኢሕአዴግ አገዛዝ ሥር እስካለን ድረስ በምርጫ ሂደት ምንም አይገኝም የሚለው አባባል ዛሬ ብቻ ሣይሆን ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ማግሥት ጀምሮ ተብሎ-ተብሎ ያለቀለት ጉዳይ ነው:: ምርጫ ሁለት-ሽህ-ሁለት ይኸንን እውነታ ለኛም ለሕዝባችንም ምንም በማያወላዳ ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ግልፅ አድርጎታል:: ከዚኽ ጥራት በተጓዳኝ ትልቅ የሁኔታዎች አሻሚ-መወሳሰብ (ፓራዶክስ) ይታያል:: የሕዝባችን የጎልውና ቀውስ ተባብሶ ከዛሬ አምስት ዓመት ዛሬ ይበልጥ አፍጦና አግጦ የሚታይበት ደረጃ ላይ እያለን የዚያኑ ያኽል ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ የጨለምተኝነቱ፣ የግራ-መጋባቱና የትጥቅ-መፍታቱ አባዜ ከዛሬ አምስት ዓመት ይልቅ ዛሬ እንዲሁ ይበልጥ አፍጦና አግጦ ያለ ሃቅ ነው:: ይኸንን አስከፊ ክስተት በወያነ/ኢሕአዴግ ላይ ሕዝባችን በሚያሣየው ድሮውንም ከእልህ የሚዋሰን ተቃውሞና ጥላቻ ጣራ መንካት ገፅታው ብቻ ወስኖ ማየት አይቻልም:: በዚያው ልክ ደግሞ በተቃዋሚዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ (ምናልባትም ከዚኽ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ) ንቀትንም የተላበሰ የእምነት ማጣት ክስተት እንዳለ መገንዘብ ይኖርብናል::

ነገር ግን ደግሞ ዛሬ ከአለንበት የተኣማኒነት ቀውስ አንፃር ሕዝባን ያለ-የሌለ ተስፋውን በተቃዋሚ ኃይሎች ላይ ጥሎ በሚሊዮንና በሙሉ ተስፋ የተንቀሣቀሰባቸው ሌሎች ወቅቶች እንደ-ነበሩ ማስታወስ ያስፈልጋል:: ከዚኽ ስንነሣ ከአለፈው ተምረን ወደ-ፊት እንጓዝ ካልን እነዚኽ የብሩኅ-ተስፋ እና የሚሊዮኖች እንቅስቃሴ ወቅቶች ለምንና እንዴት እንደ-ከሰሙ በአጭሩም ቢሆን መተንተን ያስፈልጋል:: ሁለተኛ ከዚኽ ተነስተን እኛም በሕዝባችን ፊት ተኣማኒነትን መልሰን የምናገኝበትን ሕዝባችንም መልሶ የትግሉ ባለቤት ሊሆን የሚችልበትን የትግል-ትልም (ስትራቴጂ)፣ የትግል ቅደም-ተከተል (አጀንዳ) እና የአካሄድ ጥያቄ መመርመር ይኖርብናል:: ሦስተኛ "ተኣማኒነትን ገንብቶ፣ ሕዝብን በሚሊዮን እያስቆጠሩ አንቀሣቅሶ፣...." የሚለው ውስብስብና እጅግ አስቸጋሪ የሚሆነው ትግል መልሶ መልክ ቢይዝ እንኳን ሌላ መሠረታዊ የሆነ ጥያቄ ይኖራል:: ይኽ የተንቀሣቀሰ ሕዝባዊ ማዕበል በአመራር ክፍተትም ሆነ በወያኔ የለየለት ሽብርና የከፋፍለህ-ግዛ ዘይቤ መልሶ እንዳይከስም ቀጣይነቱ የሚረጋገጥበትንም የፍልሚያ-ዘዴ (ስትራቴጂ) መቀየስ ያስፈልጋል:: ከዚያም ለመደምደም ያኽል በዚኽ ሁሉ ከአገር-ውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ (የዲያስጶራው) ሚና ምን ይሆናል? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ውይይት መደረግ ይኖርበታል::

## 1. ካለፈው ሂደት ትምሕርት፡- እየተሰባሰቡ የመበታተን፣ እየሰበሰቡ የመበተን አባዜ፤

ወያነ/ኢሕአዴግ መንግሥታዊ ሥልጣን ከተቆጣጠረ ወዲኽ ይኸንን በኅብረተሰቡ በግልፅ ከዳር-እስከ-ዳር የተተፋ መንግሥት ለማስወገድ ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ኃይሎች የጋራ ትግል እያሉ ሲንቀሣቀሱና ግልፅ ሕዝባዊ አጀንዳ አንግበው ሊፋለሙት

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel. 202 361 7162

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
ስልክ Tel/Fax 31 70 394 6132

በተደጋጋሚ ጥረት ሲያደርጉ ተመልክተናል። ከነዚኽ የጋራ ትግል ጥረቶች እስካሁን አንድኛቸውም የተፈለገውን ፍሬ አልሰጡም። ይኽ ለምን እንደሆነ ምክንያቶች ሲደረደሩ አለመተማመን፣ የሥልጣን ሽሚያ፣ ወዘተ... እየተባሉ የሚጠቀሱት ችግሮች ምን ያኽል እውነት ቢሆኑና እነዚኽን ችግሮች ብንወጣቸው እንኳን ብቻቸውን ከአለንበት ቀውስ የሚያወጡን አይሆኑም።

ጨርሶ መረሣት የሌለበት አንድ መሠረታዊ ሃቅ አለ። ተደጋግሞ እንደተባለው ትግሉ በአንድ መልኩ ሲታይ ተፃራሪ አጀንዳ ባነገቡ ሁለት አናሣ ኃይሎች መኻከል የሚደረግ ትግል ገፅታ አለው። በአንድ በኩል አናሣውና ፀረ-ሕዝቡ ወያኔ/ኢሕአዴግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ዴሞክራቱና አገር-ወዳጁ ግንባር-ቀደም ኃይል። በዚኽ ፍልሚያ ኢሕአዴግ እንደ-ድርጅት በአለው የገንዘብ አቅም ታግዞ ከዋና ከተማችን እስከ ዳር-ድንበር መንደር የተዘረጋ ድርጅታዊ መዋቅር ያለው ኃይል ነው። እንደ- መንግሥት ደግሞ የሠራዊቱ፣ የፖሊሱና የመረጃ መረቡ፣ የራዲዮው፣ የቴሌቪዥኑና የፕረስ ተቋማት ተቆጣጣሪ ከመሆን አልፎ የመንግሥት ግምጃ-ቤቶችና (ካዝናና) የአገሪቷም መሬት ሁሉ ብቸኛ አዛዥ በመሆን በሚሊዮኖች ኅልውና የፈላጭ-ቆራጭነት ሥልጣን ያለው ስብስብ ነው። ተቃዋሚው ግንባር-ቀደም ኅራ ከሕዝባዊነቱና የሚሊዮኖችን ጥቅምና ራእይ ከማንገቡ ሌላ ከነዚኽ ሁሉ የኃይል ምንጮች በአንዱም የታደለ አይደለም። ግን ደግሞ የወያኔ/ኢሕአዴግ ጥቂቶች በፀረ-ሕዝብና ፀረ-አገር ፖለቲካቸው ምክንያት መቸም ሊደርሱበት የማይችሉት ሌላ የማይናቅና ለተያዘው ፍልሚያ ወሳኝ የሆነ የኃይል ምንጭ አለው። ያም አምቅ ኃይል ታግሎ-አታጋይ ቁርጠኛ አመራር-ሰጭ ክፍል ካገኘ ለመዋደቅ፣ ለመሰዋት ዝግጁና ብቁ የሆነው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ይኽንን የጥፋት ኃይል ለመዋጋት በሰላማዊ ዘዴ እጠቀማለሁ የሚል ማንኛውም ኃይል "ሰላማዊ" ማለት እዛው በዛው "ሕዝባዊ" ማለት እንደሆነ ተረድቶ ሚሊዮኖችን ከጀርባው አሰልፎ የሚያታግል ስትራቴጂ ያስፈልገዋል።

ይኽ ካልሆነ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች ሽህ ጊዜ ግንባር፣ 'አልያንስ'፣ ኅብረት፣ መድረክ፣ ወዘተ እያልን ብንሰባሰብ ትግሉ በአናሣው ግን ደግሞ በኃያሉ ወያኔ/ኢሕአዴግና በአናሣው "ግንባር-ቀደም" ተቃዋሚ ኃይል ስለሚወሰን ከዚኽ የብረትና የሸክላ ድስት ፍልሚያ በድል አድራጊነት እንወጣለን ማለት የሚታሰብ እንኳን አይደለም። በወያኔ/ኢሕአዴግ ሥርዓት ሥር ከታዩት የተሰባሰቡ የጋራ ትግል ሙከራዎች ትምሕርት ለመቅሰም ከፈለግን ለራሣችን አቅርበን መመለስ ያለብን ጥያቄ እስከዚኽም "ትብብሮች እየተጀመሩ ለምን ይከሽፋሉ?" የሚለው ብቻ ሣይሆን ሲጀመሩ የሰበሰቡትን ይኽ ነው የማይባል የሕዝብ (አንዳንዴም ዓለም-አቀፋዊ) ድጋፍ መልሰው ለመበተን የተጠናወታቸውን አባዜ እንዴት አድርጎ መወጣት ይቻላል? የሚለው ይመስለናል።

በወያኔ/ኢሕአዴጉ ትግል ከኢዴኃቅ እስከ አማራጭ ኃይሎች፣ ከኢተፖድጎ እስከ ኢዴኃኅ (ኅብረት)፣ ከቅንጅት እስከ መድረክ የተለያዩ የጋራ ትግል ሙከራዎች በተደረጉ ቁጥር ኅብረተሰቡ "አበጃችሁ!፣ በርቱ!፣ ግፉበት!" እያለ በአለ-በሌለ ኃይሉ ከጀርባቸው ሲሰለፍ አይተናል። ከፓሪስ-አንድ በኋላ ለታኅሣሱ የአዲስ-አበባው የግዮን ሆቴል ጉባዔ ዝግጅት ሲደረግ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎች በመስቀል አደባባይ ለዚያ ጥረት ያላቸውን ድጋፍ ለማገለፅ ሰልፍ ወጥተዋል። በግንቦት ዘጠና-ሰባት ምርጫ ዋዜማ ቅንጅት በጠራውና ኅብረቱም በደገፈው ሰላማዊ ሰልፍ ከሁለት ሚሊዮን በላይ ቁጥር ያለው ሕዝብ ሲወጣ አይተናል። እንደዚኽ ሲሆን ደግሞ ከሕዝብ ድጋፍ በተጨማሪ ሌላ የሚታየው በጎ ሂደት በዓለም-አቀፍ ደረጃ ወይም በዲፕሎማሲው መስክ የሚንፀባረቀው ሁኔታ ነው። ፓሪስ-አንድ ጉባዔ ሲደረግ የአውሮጳ ፓርላማ ፕሬዝደንትና ምክትል ፕሬዝደንት፣ የፓርላማው የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የልማትና ተራድዖ ኮሚሽን ፕሬዝደንቶች ድጋፍና የማበረታቻ መልእክቶች አስተላልፈውልን ነበር። ሆኖም "ሰላማን እርቅ ጉባዔ" ብለን እዛው አዲስ-አበባ ለመሰብሰብ እንቅስቃሴ ስንጀምር ይኽንን አሳብ የኢሕአዴግ መንግሥት "በአገራችን ሰላም፣ እርቅና ዴሞክራሲ ከወዲኹ ሰፍኗል፣ የስብሰባው እቅድ የጥቂት የዲያስጶራ አክራሪ

ፖለቲከኞች ሴራ ነው" በሚል ክርክር ክፉኛ ሲቃወመው ባዕዳን አጋዦቹም በዚኽ አቋም ተሰልፈው የስብሰባውን አሳብ እነሱም ተቃወሙት፡፡ ስብሰባው ከመደረጉ ሦስት ወራት በፊት (እ.አ.አ. በሴፕቴምበር አሥራ-ዘጠኝ-ዘጠና-ሦስት ዓ/ም) ለፕሬዝደንት ክሊንተን ይኽንን ጉባዔ እንዲደግፉ ለተፃፈላቸው ደብዳቤ ኋይት ሃውስ በፅሑፍ በገለፀው የተቃውሞ አቋም "ይኽ የታቀደው ጉባዔ መልስ እሻላቸዋለሁ የሚላቸው ጥያቄዎች ከወዲሁ በለንደን በሜይ ወር ዘጠና-አንድ ዓ.ም. በተደረገው ኮንፈረንስ መልስ የተሰጠባቸው ስለሆነ..." አላስፈላጊ መሆኑን ጠቅሶ ከዚኽ ይልቅ ተቃዋሚ ኃይሎች "በሕገ-መንግሥቱ ሂደት ተሣትፎ ላይ ማተኮራቸው ይመረጣል" በማለት ከኢሕአዴግ ጎን ተሰልፎ ነበር፡፡

በተጠቀሱት ወራት ከአዲስ-አበባ አንስቶ በሌሎችም ከተሞች በተደረጉ ሰልፎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር-እስከ-ዳር ተንቀሣቅሶ ለጉባዔው መካሄድ ይፋ የሆነ ድጋፉን በማሣየቱ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች ሊያቀርቡት እንደፈለጉት "የጥቂት አክራሪ ተቃዋሚዎች እቅድ ወይም ሴራ" እንዳልሆነ በግልፅ ታየ፡፡ በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ አሜሪካኖች ብቻ ሣይሆኑ በአጠቃላይ የዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብም አቋም ሙሉ-በሙሉ ወደ-ድጋፍ ተቀየረ፡፡ የወቅቱ የፈረንሣይ ፕሬዝደንት ፍራንሥዋ ሚቴራ፣ የዓመቱ የአፍሪቃ አንድነት ሰብሳቢና የሴኔጋል ፕሬዝደንት አብዱል ዲዩፍ ለጉባዔው አዘጋጅ ኮሚቴ የድጋፍ ደብዳቤ ሲልኩ የአሜሪካ ኤምባሲ ይኽንን አሣብ የሚደግፍ መሆኑን ለማስታወቅ ይፋ መግለጫ አወጣ፡፡ በጉባዔው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንዲገኙ ጥሪ የተደረገላቸው የሰላሣ መንግሥታት፣ የሃያ-ሁለት ዓለም-አቀፍ መያዶች፣ የአፍሪቃ ኅብረት (አንድነት) ድርጅትና የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪቃ ኮሚሽን ተወካዮች ተገኝተው ድጋፋቸውን ሰጡ፡፡ ይኽ ሊሆን የቻለው ተቃዋሚዎች "በመሰባሰባቸው" ብቻ ሣይሆን ሕዝባችንን ከጎናችን እንዳሰለፍን በተግባር በማሣየታችንም እንደ-ነበር ግልፅ ነው፡፡

ግንቦት ዘጠና-ሰባትም እንደዚሁ ነበር፡፡ ሁሉም የሚያውቀው የቅርብ ክስተት ስለሆነ ዝርዝር ውስጥ መግባት የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ ሕዝብ እንደዚኽ ግልብጥ ብሎ በተቃዋሚዎች ሠፈር ሲሰለፍ ፣ ማለትም ግንባር-ቀደሙ ኃይል በእርግጥም ለትግል ከተንቀሣቀሰ ሕዝባዊ ኃይል ጋር ሲገጥም፣ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች ብርክ ይይዛቸዋል፡፡ ይኽንን "አደገኛ" ግጥምጥሞሽ ለማክሸፍና ግንባር-ቀደሙን ኃይል በመንቀሣቀስ ላይ ካለው ኅብረተሰብ ለመነጠል፣ ብሎም ሁለቱም ተያይዘው የሚዳከሙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ "ሦስትዮሽ" ሊባል የሚችል ስትራቴጂ ይከተላሉ፡፡ በዓለም-አቀፍ ተባባሪዎቻቸው ድጋፍ ግንባር-ቀደሙ ኃይል ታጋዩን ሕዝብ "ተክቶ" ብቻውን "እንዲታገላቸው" ስትራቴጂ በመንደፍ "የድርድር" አሣብ ያቀርባሉ፡፡ ተቃዋሚውን ለመከፋፈልና ለማዳከም ኅብረተሰቡን በብሔር/ብሔረሰብና በሐይማኖት ለማጋጨትና በአንዳንድ ሰርጎ-ገቦች እና በዚኽ ጎራ አመራር ላይ ባሉ ደካሞች አማካይነት አጥብቀው ይሠራሉ፡፡ ይኽ አልሠራ ካለ ወይም ደግሞ ከዚኽ በተጓዳኝ በግንባር-ቀደሙ ላይ ብቻ ሣይሆን ትግሉን ደግፈው በመንቀሣቀስ ላይ ባሉ ዜጎች ላይ በአፈናና በሽብር ውርጅብኝ ዘመቻ ይሠማራሉ፡፡

የአማራጭ ኃይሎች ምክር-ቤት በተመሠረተ ማግሥት ከጉባዔው በፊት የተንቀሣቀሰውን ሕዝባዊ ድጋፍ እያዳበረ መሄዱን ትቶ መጀመሪያ በጅሚ ካርተር ከዚያም በአሜሪካ "ኮንግረሽናል ግብረ-ኃይል ለኢትዮጵያ" በተባለው ስብሰባ አማካይነት የትም በማያደርሱና ባላደረሱ የድርድር ሂደቶች ሲሰማራ ይኽ የሕዝብ እምርታ የሚከስምበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ግንቦት ዘጠና-ሰባት ማግሥትም እነ መለስ ዜናዊ ከቁጥጥራቸው የወጣን ሕዝባዊ የትግል እምርታ ለማክሰም ከፍ ተብሎ የተጠቀሰውን "ሦስትዮሽ" ስትራቴጂ በደንብ ሲጠቀሙና ይኽንን እምርታ ሲሰብሩት አይተናል፡፡ የተቃዋሚው ጎራ አንዱ ክፍል ፓርላማ እገባለሁ ሌላው ደግሞ ቅድመ-ሁኔታዎች አቅርቦ እነዚኽ ካልተሟሉ አንገባም በሚል ሲከፋፈል በዓለም-አቀፍ አሳዳሪዎቻቸው እገዛ ይኽ "በአክራሪዎች እና በሰከኑ ተቃዋሚዎች" መኻል የተከሰተ ክፍፍል ሆኖ እንዲቀርብና ልዩነቱም እንዲሠፋ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውም ልቡ እንዲከፈል አደረጉ፡፡ አገር-አቀፍ የሆነ የተወዳዳሪዎች ጉባዔ ተደርጎ በዚኽ ጉባዔ አማካይነት ለቀጣዩ ትግል ስትራቴጂ እንዲወጣ፣ ለዚኽም የትግሉ አቀነባባሪ

አካል እንዲፈጠር ተብሎ በኅብረቱ በቀረበው አሣብ መሠረት መስከረም ሃያና ሃያ-አንድ አሥራ-ዘጠኝ-ዘጠና-ስምንት ዓ/ም ላይ ጉባዔ ተጠራ:: ከመላ አገሪቱ ከሰባት መቶ የሚበልጡ ታጋዮች አዲስ-አበባ ከገቡ በኋላ የስብሰባ አዳራሽ ጠፋ በሚል ሰበብ (እኛ ይኽ ከጠፋ ድንኳን ተክላችሁ ተሰብሰቡ እያልን ያደረግነው ውትወታ ሰሚ አጥቶ) ጉባዔው በታሰበው መልክ ሣይደረግ ሁሉም ቅስሙ ተሰብሮ ወደ-የመጣበት እንዲመለስ ተደረገ::

የተከተለውን ግራ-መጋባት ለማገዝ የኢሕአዴግ መሪዎች ቀጥለው ደግሞ ግንባር-ቀደሙ ኃይል ሕዝቡን "ተክቶ" ብቻውን እንዲፋለማቸው ከመስከረም ሃያ-ሁለት ጀምሮ የተጠራው የቤት-መዋል አድማ ተሰርዞ ችግሩ "በሰከነ መንፈስ በድርድር እንዲፈታ" አሣብ አቀረቡ:: ውይይቱን በቤት-መዋል አድማው አግዞ፣ ማለትም የተንቀሣቀሰውን ሕዝብ ከጎን አሰልፎ፣ ማካሄድ ሲያስፈልግና ሲቻል የተቃዋሚው ጎራ ተወካዮች "መንግሥት በድርድር አሣብ ተስማምቷል፣ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም ይኽንን አሣብ ደግፎ ተደራደሩ እያለ ጫና እያደረገብን ነው" በማለት እዚኽ የወያኔ/ኢሕአዴግ ወጥመድ ውስጥ ዘው ብለው በመግባት አድማው መሠረዙን አውጀው የሕዝቡን የትግል ሃሞት አፈሰሱት:: ይኽ ከተደረገ በኋላ የተጀመረው "ድርድር" ሦስት ቀናት እንኳን ሳይካሄድ፣ አንዳችም ውጤት ሣይሰጥ ተቋረጠ:: በዚኽ መልክ በወያኔ/ኢሕአዴግ ወጥመድ ውስጥ የገባው ተቃዋሚ በተዳከመበትና በተከፋፈለበት ሁኔታ የአፈናና የሽብር ስትራቴጂያቸውን በመከተል የቅንጅትን መሪዎች ብቻ ሣይሆን በያለበት የትግሉ አስተባባሪዎች ናቸው የሚሏቸውንና የሚጠረጥሯቸውን ዜጎች ሁሉ አፋፍሰው ለእስር ዳረጓቸው:: ከዚያ ተከትሎ የሆነውን እናውቃለን::

የጋራ ትግል ጥረቶች በዚኽ መልክ ሲዳከሙ ለትግሉ ወሳኝ የሆነው የኅብረተሰብ ድጋፍ ራሱ መልሶ ይበተናል:: ከአለፈው ትግል ልምድ እንደምናየው ሁለቱ በሚገጣጠሙበት ወቅት የማያወላዳ የበላይነት ይዘን የብሩኅ አዙሪት ወቅት ውስጥ እንገባለን:: በሆነ ምክንያት አንዱ መጉደል ሲጀምር ሁለቱም ተያይዘው ገደል የሚገቡበት የትጥቅ-መፍታትና የጨለምተኝነት የጥፋት አዙሪት ኅብረተሰቡን ይጠናወተዋል:: በዚኽ ላይ ትጥቅ በፈታ ኅብረተሰብ ያለ-አንዳች ተጠያቂነት የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች የሚከተሏቸው ፖሊሲዎች የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ቀውሶችን እያባባሱ የሕዝቡን ኅልውና ከዕለት-ዕለት በከፋ ሁኔታ የሚፈታተኑበት ደረጃ ላይ ይደረሳል:: ትጥቅ መፍታቱና ጨለምተኝነቱ ይባባሳል:: በሽብር ብቻ ሣይሆን በአመራር ክፍተትም የበተንነውን የሕዝብ እንቅስቃሴ እንደገና ለማሰባሰብና ሕዝቡን መልሰን የትግሉ ባለቤት ለማድረግ ስትራቴጂ ስንቀይስ የምናነግባቸው አጀንዳዎች ከበጎ ራእያችን እንጂ ሕዝባችን እየዘቀጠ ከሚሄድበት አስከፊ የሆነ የኅልውና ቀውስና ከተጠናወተው የጨለምተኝነት አባዜ የሚነሱ ስላይደሉ እሩቅ የሚያስኬዱ አይሆኑም::

## 2. የጋራ ትግል፡- ለምን ግብ? በምን አጀንዳ? በምን አካሄድ?

ጨለምተኝነት ሰፈነ፣ ኅብረተሰባችን ግራ ተጋባ፣ ትጥቅ ፈታ፣ ወዘተ.. ሲባል ሕዝባችን ለአገራችን አንድነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለፍትኅና ለሰላም ያለው ጉጉትና ራእይ ወደመ ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: አልወደመም:: እነዚኽን እሴቶች ሚሊዮኖች እንደሚጋሯቸውና ታግሎ-አታጋይ ኃይል ካገኙ ደግሞ የተፈለገውን መስዋዕትነት ከፍለው እውን ሊያደርጓቸው እንደሚመኙ ግልፅ ነው:: ነገር ግን ዛሬ በአለው ሁኔታ ይኽ ሕዝባዊ ራእይና ዓላማ ተኣማኒነት ያለው ሰብሳቢ ኃይል ስላልታደለ እንደ ስመ-ጥፉው የለንደኑ ጉባዔ ወቅት አስከፊና አደገኛ የሆነ "የኢትዮጵያዊነት ክፍተት" እየተከሰተ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: በለንደኑ ጉባዔ የታሪክ ወቅት የአገር አንድነት፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የብሔራዊ ክብር አጀንዳ ልክ እንደ-ዛሬው ሚሊዮኖች ከዳር-እስከ-ዳር ያነገቡት አጀንዳና ህልም ነበር:: ሆኖም በዚያ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያችን እጣ-ፈንታ በጥቂቶች ሲወሰን ይኽ የሕዝብ ራእይና አጀንዳ ተኣማኒነት ያለው ሰብሳቢ ኃይል አልነበረውም:: በመሆኑም የሰላሟና የዴሞክራሲዋ ብቻ ሣይሆን የአገራችን አንድነት ጉዳይ ሣይቀር በነዚኽ እሴቶች ምንም በማያምኑ ጥቂቶችና ባዕዳን ተወሰነ:: ዛሬም ቢሆን "እነዚኽ እሴቶች የሚሊዮኖች ናቸውና ..." እያልን የምንዘናጋበት ምንም ምክንያት የለም:: የሚሊዮኖች ህልም በጥቂቶች

ሴራ ለጊዜውም ቢሆን እንደ ለንደኑ ሊጠለፍ ይችላል። ደጋግመን ለመጠቆም እንደ-ሞከርነው ዛሬም እንደ ትላንቱ በግንቦት ዘጠና-ሰባት ሳቢያ ሕዝባችን ጥማቱን ብቻ ሣይሆን ብቁነቱን ያሣየባቸው የአንድነት፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የፍትኅ እሴቶች አስተማማኝ የሆነ ሰብሳቢ ኃይል የላቸውም። ይኸ ክፍተት ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት ለመቋቋም በሕዝባችንም ፊት ሆነ በማንም ይሁን በማን ዓይን ተኣማኒነት ያለው ሠፊ የጋራ መድረክ የማቋቋሙ ጉዳይ እጅግ አጣዳፊ ተግባርና አገራዊ ግዴታ የሚሆነውም ለዚኸ ነው እንላለን። ይኸንን አገራዊና ታሪካዊ ተልዕኮ ለመወጣት መጀመሪያ ግልፅ በሆነ ስትራቴጂያዊ ግብ ዙሪያ መሰባሰብ ቁልፍ ጉዳይ ይሆናል። ከዚያ ቀጥሎ ለዚኸ ግብ እውንነት ታግሎ - ለማታገል ለሕዝባችን የሚደረጉ የቅስቀሳ ጥሪዎች በምን ዙሪያ መቃኘት ይኖርባቸዋል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር ያስፈልጋል።

## ሀ. ስትራቴጂያዊ ዓላማችንን በግልፅ የማስቀመጥ ጉዳይ፤

በምርጫ ዘጠና-ሰባት ወቅት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ለሕዝብ አቅርቦት የነበረው አማራጭ ሰነድ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ ወዘተ.. ጉዳዮች ላይ ብዙ ቁም-ነገሮችን የያዙ ነጥቦች ቢካተቱበትም ይኸ አማራጩ ሰነድ ግማሽ አካል ብቻ ነበር። በዚኸ ሰነዳችን ላይ የትግላችን ዋና ዓላማ አንድነቷ በተረጋገጠ ኢትዮጵያ መድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲን የሚያፀድቅ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መገንባት እንደ-ሆነ በግልፅ ተቀምጧል። ይኸ የተቀደሰ አገራዊ ዓላማ እውን እንዲሆን የኢሕአዴግ መሪዎች በሕዝብ ትግል ከጥፋት ሂደታቸውና ይዞታቸው እንዲገቱ ከተደረገ በኋላ አንድ “የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አገር-አቀፍ ጉባዔ” አስፈላጊ እንደሚሆን በተደጋጋሚ ተገልጿል። እንዲኸ ዓይነቱ ጉባዔ በአጠቃላይ በአገራችን አሉ የሚባሉ የፖለቲካ ኃይሎች፣ የሲቪኩ ማኅበራትና የነፃው ፕረስ ተወካዮች፣ ከየአካባቢው የሚመጡ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሐይማኖት አባቶች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የሙያና ሌሎች ማኅበራት ስብስቦች፣ ምሁራን፣ ወዘተ.. የሚሣተፉበትና ተወያይተው የአገራችንን እጣ-ፈንታ የሚቀይሱበት ጉባዔ መሆን እንደሚኖርበት በሰነዱ በደንብ ተሰምሮበታል።

አገራችንን ወደ-ዴሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እናሸጋግር ካልን የዚኸ ኃላፊነት በዚኹ ጉባዔ ለሚመረጥ “የዴሞክራሲያዊ-ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) ኮሚሽን” መተው እንዳለበት፣ ትርጉም ያለው ብሔራዊ እርቅ ወርዶ የተረጋጋ ኅብረተሰብ እውን ለማድረግ ደግሞ በዚሁ ጉባዔ የሚሰየም “የብሔራዊ እርቅ ኮሚሽን” እንደሚያስፈልግና የነዚኸን አካላት አሠራር፣ አባላትና ተግባራት፣ ወዘተ.. በተመለከተ በሰነዳችን ላይ በሠፊው ተብራርቶ ተቀምጧል። ዛሬም ቢሆን በዕለት-ተለት ትግል ተጠምደን “ወዴት እየሄድን ነው?” በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ምንም ዓይነት ውዥንብር እንዳይፈጠር ከፈለግን የትግላችን መቋጠሪያ ይኸ በአገራችን ምድር የሚሰየም “የዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባዔ” እና ከሱም የሚፈልቁት እነዚኸ ሁለት ኮሚሽኖች እንደ-ሆኑ ከወዲሁ አስረግጦ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ይኸንን ጥያቄ በግልፅ መመለስና ይኸንን አጀንዳ ማስቀመጥ ማን ይሰብሰብ? ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ “ለጠንካራ፣ ለዴሞክራሲያዊትና አንዲት ኢትዮጵያ የቆሙ ኃይሎች” የሚል የማያሻማ መልስ እንድንሰጥ ይረዳናል። ዛሬ ባለው ውዥንብር ይኸንን ዘላቂ ዓላማ ለጊዜው ወደ-ጎን ትተን የመሰባሰቢያው መድረክ “ፀረ-ወያኔነት” ብቻ እንዲሆንና የአገራችን አንድነት ጉዳይ ልክ እንደ-ማኅበራዊና የኤኮኖሚ ጉዳዮች “በይደር” እንዲቀመጥ ሙከራዎች እንደሚደረጉ እናውቃለን። “ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ” ይባል የነበረው ስብስብ ሲቋቋም በርካታ የአገራችን ዴሞክራቶች ድጋፍ የሰጡት ከዚኸ የተዛባ ስሊት ተነስተው እንደ-ነበረ ይታወቃል። እንዲኸ ዓይነቱ አንዱ ወደ-አራምባ ሌላው ወደ-ቆቦ የሚያመላክትበት ስብስብ የትም የሚያደርስ አልነበረምና የትም ሣይደርስ ከሰመ። ከዚኸ በመነሣት ምንም ለጊዜው የታመቀ ቢመስልም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ጉዳይ የሚሊዮኖች ራእይ ነውና የቅድሚያ-ቅድሚያ መስጠት ያለበት ተግባር ብሔር/ብሔረሰብ፣ ሐይማኖት፣ አካባቢ፣ ወዘተ.. ሳይባል ለዚኸ አገራዊ አጀንዳ የቆሙ ኃይሎችን የማሰባሰቡ ጉዳይ እንደሆነ በግልፅ መሰመር ይኖርበታል። እርግጥ ይኸ ማለት ከዚያ በኋላ ሙሉ-በሙሉ

የእኛን ሕዝባዊና አገራዊ አጀንዳ ካላነገቡ ፀረ-ወያኔ/ኢሕአዴግ ኃይሎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት፣ ድርድር፣ ወዘተ… አይኖርም ማለት አይደለም:: መጀመሪያ እራሣችንንና ሕዝባዊ ትግሉን አጠናክረን ከዚያ በሙሉ-ልብነት እነዚኽ ኃይሎች በያዙት አጀንዳ ውይይት ማድረግ ይቻላል:: እንዲኽ ዓይነቱ በግልፅ የተከሰተውን **የኢትዮጵያዊነት ክፍተት** ለመድፈን የተሰባሰበ ኃይል ሚሊዮኖችን መልሶ አንቀሣቅሶ የትግሉ ባለቤት ለማድረግና እዚኽ አገራዊና ዴሞክራሲያዊ ግብ ለመድረስ አሁንም ካለፈው ትምሕርት ቀስሞ ከአለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የተነደፈ የትግል አጀንዳ ያስፈልገዋል:: ይኽ ደግሞ የተቃዋሚውን ጎራ አመራር "ተአማኒነት መልሶ የመገንባት" ወደሚለው ወሳኝ ጥያቄ ያመጣናል::

## ለ. ተአማኒነት ያለው አመራር ለመገንባት፡- በምን አጀንዳ? ምን አካሄድ?

የአጀንዳና የተአማኒነት ነገር ሲነሣ ከሁሉ በፊት መስመር የሚኖርበት ቁም-ነገር አንድ ሕዝብ ምንም ከክቡርም ክቡር ቢሆኑ ለዴሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለነፃ ምርጫ፣ ወዘተ.. በሚሉ እሴቶች ዙሪያ ሁል-ጊዜም በማንኛውም ሁኔታ በሚሊዮን እየተቆጠረ መንቀሣቀስ አለመቻሉ ነው:: በነዚኽ ክቡር መፈክሮች ዙሪያ ከተንቀሣቀሰ በኋላ በሽብርና በአመራር ክፍተት መልሶ ትጥቅ ሲፈታና በኅብረተሰቡ ጨለምተኝነት ሲሰፍን እነዚኽ በትግሉ አፍላ ወቅት ኅብረተሰቡን ከዳር-ዳር ያንቀሣቀሱ የነበሩ እሴቶች በሚከሰተው አዲስ ሁኔታ ወይም አስተጋቦ ከሰማይ የራቁ አጀንዳዎች እንደሚሆኑ መረዳት ያስፈልጋል:: ይኽ ግልፅ እንዲሆንልን ወደ-ግንቦት ዘጠና-ሰባት ቅልበሣ ማግሥት ተመልሰን ያኔ አካሄዳችን ምን እንደ-ነበረ ማየትና ከሱ ትምሕርት መቅሰም ይኖርብናል:: ቅልበሣውን በተከተሉት ሣምንታትና ወራት 'የሕዝብ ድምፅ ይከበር' እያልን በቅልበሣው የፖለቲካ ገፅታ ላይ ያተኮረ ትግል አድርገን ሕዝባችንን ለተወሰነ ጊዜ አንቀሣቅሰን እንደ-ነበረ ይታወቃል:: ይኽ ግን ሕዝባዊ ትግሉም አፈናውና ሽብሩም ተያይዘው በአፍላ ደረጃ በነበሩበት የትንንቅ ወቅት ነበር:: የአመራር ክፍተት ተከስቶ፣ ሕዝቡም (በተለይ ወጣቱ) ብቃት ያለው አስተባባሪና መሪ ኃይል አጥቶ ተራ-በተራ እየተነሣ ተራ-በተራ ከተመታ በኋላ የትግሉ ቅስም ተሰበረ:: ጅምላ ግድያው፣ አፈሣውና ሽብሩም ቀልብ በሚስብ መልካቸው "አላስፈላጊ" ሆነው ጋብ አሉ:: ነገር ግን የሕዝብ ድምፅ ተዘረፈ ማለት ኅብረቱም ሆነ ቅንጅቱ ለሕዝባችንና ለአገራችን ይበጃሉ ብለው ያቀረቧቸው ሕዝቡም ይሆኑኛል፣ ይስማሙኛል ያላቸው በጎ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ አማራጮችም ተዘረፉ ማለት ነበርና ኢሕአዴግ በአጥፊ ፖሊሲዎቹ ቀጠለ:: በሽህና በብዙ አሥርተ-ሽህዎች ሰለባዎች ተወስኖ የነበረውና እየደበዘዘ የሄደው የፖለቲካ አፈና በአመቻቸላቸው ሁኔታ የወያኔ/ኢሕአዴግ መሪዎች እንዳመቻቸው በተግባር በሚተረጉሟቸው የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲዎች ሣቢያ ይኽ ቅልበሣ "በአማራጭ ዝርፊያ" ገፅታው እየጎላ ከሽዎች ከአሥርተ-ሽህዎች ግንባር-ቀደም ታጋዮች ዘልቆ ሚሊዮኖች በዕለት-ተለት ኑሯቸው የሚቀጡበት፣ ኅልውናቸው ከጥያቄ ውስጥ የሚገባበት ከባድ ቀውስ እየሆነ መጣ::

ሆኖም ተቃዋሚ ኃይሎች እነዚኽን የሕዝባችንን ጉረሮ አንቀው የያዙትን ችግሮች እያነሱ፣ በእነሱም አኳያ **ልክ በምርጫው ዘመቻ ወቅት ያደርጉ እንደ-ነበረው** ያላቸውን አማራጭ እያቀረቡ ከሕዝቡ ብሶት እየተነሱ ተንቀሣቅሰው ሕዝቡን ለማንቀሣቀስ አልሞከሩም:: ከዚኽ ይልቅ በነዚኽ ለሕዝባችን ኅልውና ወሳኝ በሆኑ በጎ አማራጮች ዙሪያ የሚደረገውን ትግል የቧልት ሁለት-ሽህ-ሁለት ምርጫ ዘመቻ እስኪደርስ ድረስ በይደር አስቀምጠው በኅልውናው ጥረት ተይዞ "ዕድቁ ቀርቶብኝ በወጉ በኮነነኝ" የሚለውን ኅብረተሰብ ለነፃ ምርጫ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለተቋማት ግንባታ ተነስ ታገል በሚሉ ራእይ-ተኮር መፈክሮች ዙሪያ ለማንቀሣቀስ ሞከሩ:: ነገር ግን ይኽ የሕዝቡን ተጨባጭ የኑሮ ችግሮችን "ወያኔን ከጣልን በኋላ እንደርስባቸዋለን" በሚል ስሌት በይደር አስቀምጦ "ዛሬ ለመብህ፣ ነገ ለኅልውናህ!" የሚል እንግዳ ጥሪ ጭራሹን የጨለምተኝነቱን፣ የትጥቅ መፍታቱንና የተቃዋሚው ጎራ አመራር በሕዝባችን ፊት ያለውን ተአማኒነት የማሽቆልቆል ሂደት ከማገዝ ሌላ ምንም የፈየደው ነገር አልነበረም::

እንደዚኹም በመሆኑ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ካለፈው ትምሕርት ቀስመው እንደገና ለጋራ ትግል ይሰባሰባሉ ሲባል ወሳኙን የሕዝብ ኃይል መልሰው ለማንቀሣቀስ የሚያስችላቸውን አጀንዳ እናንግብ ካሉ ከዚኽ "ወረድ" ብለው በሕዝባችን ፊት ተጨባጭ የሆኑ የትግል መፈክሮች ማንገብ ይጠበቅባቸዋል። ይኽ ማለት አንደኛ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ቀስ-በቀስ ብሶታቸውን እያነገቡ እንዲንቀሣቀሱ፣ ሁለተኛ ደግሞ ተቃዋሚ ኃይሎች ይኽንን ትግል የመቀስቀስ ብቻ ሣይሆን የማስተባበርም ኃላፊነት አለባቸውና ሁሉም "ብሶትህ ብሶቴ" እያለ እንዲተጋገዝ፣ ሦስተኛ ለነዚኽ ሁሉ ችግሮች ዘላቂ መፍትኄ የሚገኘው ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ሲኖሩ በመሆኑ ሁሉም በአንድ አቅጣጫ እየገፋ ለሥርዓት ለውጥ እንዲታገል መቀስቀስና ታግሎ-ማታገል ያስፈልጋል ማለት ነው። ግን ደግሞ በትግሉ አጀንዳ ዙሪያ ስምምነት ላይ መድረሱ ብቻውን በቂ አይሆንም። ከዚኽ አልፈን በሕዝባዊ መፈክሮቻችንና አጀንዳችን ዙሪያ ዛሬ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ይኽ እንቅስቃሴ ደረጃ-በደረጃ ሠፊ፣ የተባበረና በአንድ አቅጣጫ የሚገፋ ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ስለሚሆንበትም ሁኔታ መወያየት ያስፈልጋል። ይኽ ደግሞ ተኣማኒነት ያለው አመራር ቀስ-በቀስ ለመገንባት ምን ዓይነት አካሄድ እንከተል? ወደሚለው ጥያቄ ያመጣናል።

ሕዝባዊ ትግል ስንል እንደ ግንቦት ዘጠና-ሰባት ማግሥት ዛሬ ሕዝቡ ሆ ብሎ ወጥቶ በያለበት የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፎች፣ የሥራ ማቆም አድማዎች፣ ወዘተ.. ይደረጉ የምንል ከሆነ ይኽ በአጭር ጊዜ የሚሆን አይደለም። እርግጥ ከአንድ ሁለት ወራት ጀምሮ በቱንዚያ፣ በግብፅና በቀረው አረብ ዓለም የተነሣሱት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች "በእኛስ አገር?" የሚሉ ጥያቄዎችን እንዳጫሩና ሕዝባችንም የነዚኽን ንቅናቄዎች አርአያ ተከትሎ እንዲነሣ ጥሪዎች እየተደረጉ እንደሆነ እየታዘብን ነው። የግብፅን ምሣሌ ብንወስድ ዛሬ እዚኽ የደረሰው የወጣቱ "ሸባብ የአፕሪል ስድስት ወጣቶች እንቅስቃሴ" የተባለው ስብስብ ከአራት ዓመታት በፊት የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ከዕለት-ዕለት እየከፋ መሄዱን ለመቃወም ተደራጅቶ ሲሠራ የቆየ ስብስብ እንደሆነ እናውቃለን። የቱኒዝያውም ቢሆን የትግሉ መለኮስና ሂደት ከዚኽ ከሕዝብ ተጨባጭ ከሆነ የኀልውና ጥያቄ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ታይቷል። የኑሮ ሁኔታ እየከፋ መሄድ ጥያቄ ከተነሣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚገኝበት የመከራና የሰቆቃ ሁኔታ ከነዚኽ አገሮች ሕዝቦች እጅግ የከፋ እንደሆነ ይታወቃልና ይዋል-ይደር እንጂ በኛም አገር ቢሆን ሕዝባችን በቃኝ፣ መረረኝ ብሎ በዚኽ ግፈኛ አገዛዝ ላይ መነሣቱ አይቀሬ የታሪክ ግዴታ እንደሆነ እናምናለን። ዛሬ በአለው ተጨባች ሁኔታ እንደ ቱኒዝያና ግብፅ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ለመነሣሣት ለጊዜው አስቸጋሪ ይሆናል ስንል በየካቲት ስድሣ-ስድስትም ሆነ በግንቦት ዘጠና-ሰባት ይኽ ነው በማይባል ወኔ ተንቀሣቅሶና አይከፍሉ መስዋዕትነት በከፈለበት ትግሉ ነፃ ለመውጣት ፍላጎቱም ብቃቱም እንዳለው በገሃድ ያሣየውን ሕዝባችንን የመነሣሣትና የመዋደቅ ፍላጎት አጣጥለን ለማቅረብ እንዳልሆነ ግልፅ መሆን አለበት። ሕዝባችን ለዚያ አሁንም ፍላጎቱም ሆነ ብቃቱ አለው። ዋናው ጥያቄ ይኽ ሣይሆን ሕዝባችን የሚያልመውን እንዲኽ ዓይነቱን ሕዝባዊ ማዕበል በተቻለ ፍጥነት ለመቀስቀስ፣ መቀስቀስ ብቻም ሣይሆን ለድል ለማብቃት እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች እንዴት ብቃት ይኑረን?፣ እንዴት እንዘጋጅ ወይም እንንቀሣቀስ? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው። በእኛ ግምት ለዚኽ እውንነት በሁለት አቅጣጫዎች መሥራት ይኖርብናል ብለን እናምናለን።

አንደኛ ልክ እንደ ምርጫ ዘመቻው ወቅት በተጨባጭ አማራጮች፣ የሕዝባችንን ጉረሮ አንቀው በያዙት የኀልውና ቀውሶች ዙሪያና እነዚኽን ከዴሞክራሲ ጥያቄ ጋር እያያዙ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፤ በገበሬው፣ በወጣቱ፣ በሥራ-አጡ፣ በነጋዴው፣ ጥሪት-እፍሳሹ (ኢንቬስተሩ)፣ በሠራተኛው፣ በምሑሩና በባለሙያው፣ ወዘተ.. ዙሪያ ከተቻለ በትናንሽ ስብሰባዎች አማካይነት ጭምር በችግሮቹና በመፍትኄዎቻቸው ላይ ያተኮሩ ውይይቶችና ቅስቀሣዎች ማካሄድ የሚጠቅም ይመስለናል። በዚኽ አካሄድ ላይ ስምምነት ካለ በተለይ እውቅና አግኝንተው የሚንቀሣቀሱ ተቃዋሚዎች በበኩላቸው ለዚኽ ትግል

የሚያደረጉትን አስተዋፅዖ ለማጎልበት ከደፈና ቅስቀሣ ዘልቆ የሚሄድና አሳማኝ የሚሆን ቅስቀሣ ለማካሄድ መሠረታዊ የሆነ የአደረጃጀት ማስተካከልን ይጠይቃል፣ ያስፈልጋልም።

አሁን በግልፅ እንደሚታየው የኢሕአዴግ መሪዎችና ካድሬዎች የሚያራምዷቸውን የጥፋት ፖሊሲዎች "ቀስ-በቀስ አገሪቱን ወደ-ምድራዊ ገነትነት እየቀየሩ ያሉ ፖሊሲዎች ናቸው" ብለው ለማሣመን የሆነ-ያልሆነ ስታቲስቲክስ ሣይቀር መደርደር ይቃጣቸዋል። በየመስኩ ተግባር ላይ እየዋሉ ያሉ አጥፊ ፖሊሲዎች ሽንጣቸውን ገትረው ለመደገፍና ሕዝብን ለማደናገር የሰለጠኑና የሚሉትን የሚያውቁ "ተከራካሪዎች" አፍርተዋል። በምርጫ ወቅት ካቀረቧቸው "አማራጮች" በተጨማሪ አሁን ደግሞ "ልማትና ትራንስፎርሜሽን" ብለው በአጥፊ የማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ (ሶስዮ-ኤኮኖሚክስ) ፖሊሲዎቻቸው ዙሪያ ድጋፍ ለማሰባሰብ በሕዝባዊ ስብሰባዎችና በሌሎች መድረኮች ያላሰለሰ ቅስቀሳ እያካሄዱ ናቸው። በተቃዋሚው ጎራ ያለው ሥዕል ከዚኽ ጨርሶ የተለየ ነው። እርግጥ በየ-አምስት ዓመቱ የምርጫ ዘመቻ ሲጀመር ተቃዋሚ ድርጅቶች በሚያቀርቧቸው አማራጮች ዙሪያ በየመስኩ ብቃት ያላቸው ዜጎች ከኢሕአዴግ ተወካዮች ጋር ሲከራከሩና የሕዝብን የማያወላዳ አመኔታ ሲጎናፀፉ አይተናል። ችግሩ እነዚኽ ወገኖች የምርጫው ዘመቻ ሲያከትም ደብዛቸው ጠፍቶ እስከ ቀጣዩ ፋይዳ-ቢስ ምርጫ ድረስ ሜዳውን ከፖለቲካ ጥያቄ ሌላ እምብዛም ለማይታያቸው የፖለቲካ መሪዎች የመልቀቁ አባዜ ነው። ይኽ የእይታ ችግር ብቻ አይደለም። "ከእንግዲኽ ወደ-ቁም-ነገሩ እንግባ" ብለን ሕዝባችንን በነዚኽ ተጨባጭ ጭንቀቶቹ ዙሪያ አማራጮቻችንን አንግበን በየኅብረተሰቡ ክፍል እየገባን ተንቀሣቅሰን እናንቀሣቅስ ብንልም ከዚኽ የእይታ ለውጥ ጋር መሠረታዊ የአደረጃጀት ለውጥም ያስፈልገናል።

የተቃዋሚ ኃይሎች አደረጃጀት ከልማዳዊው አሠራር ያልተላቀቀ፣ የፖለቲካ መሪ ከተባለ "ሁሉም በሁሉም መስክ አዋቂ" ሆኖ የሚቀርብበትን አካሄድ የሚከተል ነው። ድርጅት ሲቋቋም ፕሬዝደንት፣ ም/ፕሬዝደንት፣ ዋና-ፀሐፊ፣ የውጭ ግንኙነት፣ የድርጅት-ጉዳይ ኃላፊ፣ ገንዘብ ያዥ፣ ወዘተ.. እና ግፋ ቢል የወጣቶችና የሴቶች ተጠሪ ይባላል እንጂ በኅብረተሱ ውስጥ አፍጥጠው-አግጥጠው ለሰፈኑ ቀውሶች ራሱን የቻለ ተጠሪ ተብሎ የሚሰየም አካል (ክፍል) እምብዛም የለም። (ኅብረቱ ሲመሠረት ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት በመስጠት መዋቅሩ ውስጥ በልዩ ልዩ ዋና-ዋና ዘርፎች ላይ ትኩረት ሰጥተው ጥናት የሚያደርጉና አቀናብረው የሚያቀርቡ አካላት ተቋቁመው ነበር።) ይኽ አካሄድ የኢሕአዴግ መንግሥት በየመስኩ የሚከተላቸውን ፖሊሲዎች በተጨባጭ ለመቃዎምና አማራጮችን አሳማኝ በሆነና በተለይ ደግሞ ተከታታይነት ባለው ዘዴ ለማስተላለፍ እንቅፋት መሆኑ እስካሁን ታይቷል። ከዚኽ በመነሣት የተቃዋሚ ድርጅቶች አደረጃጀታቸውን ልክ እንደ-መንግሥት አድርገው የእርሻና የመሬት ይዞታ መስክ ይሁን የፋይናንስ ፖሊሲ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ይሁን የሕክምና፣ የትምሕርት ይሁን የአካባቢ ጥበቃ፣ የወጣቶች ይሁን የሴቶች ጉዳይ፣ የሥራ-አጥነት ይሁን የመናጢ ድህነትና ጎዳና-ተዳዳሪነት ችግር፣ ጧሪ-ያጡ አዛውንት ጉዳይ ይሁን አሳዳጊ-አልባ የሆኑ ሕፃናትና ልጆች፣ የመከላከያ ይሁን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ ወዘተ.. ባለቤት እንዲኖራቸው በጥላ መንግሥታዊ ይዞታ "ሻዶ ካቢኔ" ዓይነት መደራጀት ያስፈልጋቸዋል። በዚኽ መልክ በየመስኩ ተጠሪዎች በመሰየም የምርጫ ዘመቻን ወቅት በጎ አካሄድ ቢቀጥሉበት በተጨባጭ በአማራጮች ዙሪያ ለሚደረገው ትግል ትልቅ የወደ-ፊት እርምጃ ይሆናል። ለእንደዚኽ ዓይነቱ አካሄድ እውንነት በአገር-ውስጥ በይፋ የሚንቀሣቀሱ ኃይሎች ከፍተኛ አስተየዋፅዖ ማድረግ ቢችሉም ይኽ ተግባር ለእነሱ ብቻ የሚተው አይደለም። ይኽ ደግሞ ወደ-አካሄዳችን ሁለተኛና "አንቀሣቃሽ ኃይሎች ላይ ማተኮር" ወደ-ሚለው ቁልፍ ዘርፍ ያመጣናል።

የምናቀርባቸው ሕዝባዊ አማራጮች ምን ያኽል በጎና ተጨባጭ ቢሆኑም ወደ-ሕዝቡ ደርሰው የትግል ቀስቃሽ መሣሪያ እንዲሆኑ በማያባሩ "ፀረ-ወያኔ" መግለጫዎች አማካይነት የትግል ጥሪ ማስተጋባት ብቻውን እሩቅ አይወስደንም። አመራር መስጠት ማለት ጥሪ ከመወርወርም አልፎ ከፍ ብለን በጠቀስናቸው የተሰበጣጠሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ

በተቀነባበረና በተደራጀ መልክ ተሠማርተው እነዚኽ ክፍሎች ለትግል እንዲነሣሱ ጥንቃቄ በተሞላበት - ማለትም ዛሬ በአለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አስገዳጅነት ድርጅታዊ ሥራ በኅቡዕ የሚሠሩ ጥቂትም ቢሆኑ የተዋቀሩ ዜጎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው፡፡ ይኽ ዓይነቱ አንቀሣቃሽ ኃይሎች ላይ የሚያተኩር አሠራር አንደኛ እራሱ ቅስቀሣው በቀላል ቋንቋ ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲደርስ ይረዳል፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ዜጎች በቅስቀሣው ተደፋፍረው ወደ-ትግሉ እንዲገቡ ከይፋ አመራሮች በተጓዳኝ የሚሠራ የእንቅስቃሴ እምርታ የሚፈጥርና ቀጣይነቱንም ለማረጋገጥ የሚችል ግንባር-ቀደም ኃይል ይኖራል ማለት ነው፡፡ ይኽ "አንቀሣቃሽ ኃይል" በአንድ በኩል አስካሁን ድረስ በአገር-ውስጥ ወጣቱንና ተማሪውን ጨምሮ "የሕዝብ ድምፅ ይከበር"፣ "ዴሞክራሲና ተጠያቂነት ይኑር"፣ "ነፃው ፕረስ አይታፈን"፣ "የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ" እያለ አሁን የቀዘቀዘውን ትግል በግንባር-ቀደምትነት ሲያካሂድ ከነበረው ኃይል ሊመለመል ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ከሚገኙና የዚያን ኅብረተሰብ ብሶትና ችግር ዕለት-በለት እየተጋሩ ከሚኖሩ ያንን ክፍል ለትግል ለመቀስቀስ ከሚሹ "ውስጥ-አዋቂ" ዜጎች መኻከል የተቻለውን ያኽል ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ በዚኽ  መልክ ቀስ-በቀስ በአገራችን የሕዝብ ትግል ለመቀስቀስ የሚደረገው ትግል ምንም እንኳን እጅግ ሠፊ፣ አዳጋች፣ እልህ-አስጨራሽና ገንዘብ፣ ጊዜ ጉልበትና ጥንቃቄ የተሞላበት ቅንብር የሚጠይቅ ቢሆንም ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ከዚኽ በተጨማሪ ከአለፈው ትምሕርት ቀስመን ወደ-ፊት እንራመድ ካልን ይኽ የተነሣሣ ሕዝባዊ ትግል ማዕበል መልሶ እንዳይከስም ምን እንድርግ? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ ይኽ ደግሞ የትግሉን ቀጣይነት ማረጋገጥ ወደ-ሚለው  ወሳኝ ነጥብ ያመጣናል፡፡

## ሐ. የትግሉን ቀጣይነት ስለ-ማረጋገጥ፤

ከፍ ብሎ እንደ-ተተቀሰው የግንባር-ቀደሙና የሠፊው ሕዝብ ትግል ሲገጣጠሙበት ወያነ/ኢሕአዴግ በአለ-በሌለ ኃይሉ ይኽንን ግጥጥሞሽ ለመስበር "ሦስትዮሽ" ባልነው ስትራቴጂው ሲሰማራ አይተነዋል፡፡ ነገም ከዚኽ ሌላ-ነገር አንጠብቅም፡፡ እርግጥ ገጣቢትን አይተናልና በእሣት አንጫወትም ካልን የኢሕአዴግ መሪዎች እንደገና ሕዝቡን በትኑና "እንደራደር" ቢሉን አድማጭ ላያገኙ ይችላሉ፡፡ የተቃዋሚውን ጎራ እንከፋፍል ብለው ቢነሱ በሕዝባዊ ጎራ ፀንቶ የቆመው ኃይል ከሃዲዎቹንና ሰርጎ-ገቦቹን አንጓሎ አውጥቶ ሕዝቡ እንዲተፋቸው ማድረጉም እስከዚኽ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡  እነዚኽን ሁለት ፀረ-ሕዝብ ስትራቴጂዎች ለማክሸፍ የሰከነ፣ ብስለት ያለውና በሕዝብ ወገንነቱ የፀና አመራር ካጋጠመው ወያኔ/ኢሕአዴግ ይኽንን አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል በ"አክራሪነት" እና በ"ነውጠኝነት" ወንጅሎ በሽብር ተግባር ላይ እንደሚሠማራና ከዚኽ እኩል ደግሞ ይኽንን ሕዝባዊ ትግል በብሔር/ብሔረሰብና በሐይማኖት ከፋፍሎ ለማክሰም እንደሚሞክር መጠበቅ ይኖርብናል፡፡

የሽብርን አደጋ ለመከላከል ሁለት የሚተጋገዙ ተግባራት ይኖሩናል ብለን እናምናለን፡፡ ከሁሉ መጀመሪያ በሽብር ጎዳና ከመሠማራታቸው በፊት የኢሕአዴግ መሪዎች ሁለት ጊዜ እንዲያስቡ ለማድረግ በአገራችን በግንቦት አሁን ደግሞ በቱንዝ፣ በግብፅና በቀረው የአረቡ ዓለም እንደ-ታየው ሕዝቡ ሕዝቡ በሽህና በአሥርተ-ሽህ ሣይሆን በመቶ ሽዎችና በሚሊዮኖች እየተቆጠረ፣ ተራ-በተራ ሣይሆን በአንድ ጊዜና በአገር-አቀፍ የሚነሣበትና እነሱንም የሚከፋፍል፣ በዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ፊትም አገዛዛቸው ምንም ተቀባይነት እንደሌለው በሚያሣይ ስፋት መንቀሣቀሱ ወሳኝ ነው፡፡ ይኽ በራሱ ፀረ-ሕዝቦቹ በሽብር ጎዳና እንዳይሠማሩ ሁኔታዎችን የሚያመቻች "የቀድሞ-መከላከያ" እርምጃ ቢሆንም በሱ ብቻ መተማመን የሚቻል አይመስለንም፡፡ በመሆኑም የዚኽ አካሄዳችን ሁለተኛ ዘርፍ "አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ያዥ" እንደሚባለው ይኽንን ሊከሰት የሚችል የሽብር ዘመቻ ለመቋቋምና ለሕዝባዊ ትግል ቀጣይነት-ያለው አመራር ለመስጠት ሁኔታዎችን ማመቻቸት በምንም ዓይነት ሊታለፍ የማይችል ተግባር ነው፡፡ በግንቦት ማግሥት ሕዝባችን ከባድ መስዋዕትነት እንዲገብር ካደረጉት ስህተቶች አስፈላጊውን ትምሕርት ቀስመን ወደ-

ፊት እንራመድ ካልን በአገር-ውስጥ በይፋና በሕጋዊ መንገድ ከሚካሄደው ትግል በተጓዳኝ የመጣ ሽብር ቢመጣ የሕዝቡን ትግል ማስተባበርና መምራት የሚችል ወያኔ/ኢሕአዴግ በምንም ሊደርስበት የማይችል ኅቡዕ የሆነ መሪ አካል ከወዲሁ ማዋቀር ጨርሶ የማይታለፍ ተግባር ነው ብለን እናምናለን።

እንዲኽ ዓይነቱ አካሄድ በፅንሰ-አሣብ ደረጃ አስፈላጊነቱ የማያጠያይቅ ቢሆንም ወደ-ተግባር እንዲተረጎም በርካታና ውስብስብ ጥያቄዎችን አንስቶ በበቂ መመለስ ያስፈልጋል። ማንና እንዴት በኅቡዕ ይደራጅ? የሚለው ጥያቄ ሠፊ የሰከነ ውይይት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። ከወዲሁ ግን አንድ ነገር ማለት ይቻላል። ከፍ ብለን በኅብረተሰቡ ውስጥ መልሰን ተኣማኒነት ለመገንባት "አንቀሣቃሽ ኃይል" ያልናቸው ሊጫዎቱ የሚችሉትን ሚና ጠቁመናል። የቀጣይነትና የኅቡዕ አደረጃጀት ጉዳይም ሲነሣ እነዚኽ ዜጎች ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል። በመሆኑም ከነዚኽ "አንቀሣቃሽ ኃይሎች" መኻከል በቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ቢሆኑም በገበሬው፣ በሠራተኛው፣ በተማሪው፣ በወጣቱና በነጋዴው፣ በታክሲ-ነጅው፣ በመንግሥት ሠራተኛው፣ በሴቶችና በሌላው ዴሞክራሲያዊ ኃይል አካባቢ በኅቡዕ የተደራጁና ተቀነባብረው የሚሠሩ ዜጎች ማፍራት ለትግሉ ግብ መምታት ወሳኝነት ይኖረዋል።

የሕዝባችንን ትግል ለማክሸፍ ሌላው የሚጠቀሙበት የከፋፍለህ-ግዛ ስትራቴጂያቸውም ቢሆን ከሽብሩ የማይተናነስ ፀረ-ሕዝብ አጀንዳ እንደሆነ ሣይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። እንዲያውም በአረቡ ዓለም በመካሄድ ላይ ካሉት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች የምንማረው አንዱ ቁም-ነገር ግልፅ በሆነ ሁኔታ ሕዝብ በአንድ ላይ ሆኖ በአፋኝና ሙሰኛ መሪዎች ላይ ሲነሣ ገዥዎች በለየለት ሽብር እንሰማራ ካሉ ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ እንዳለፉት ዘመናት ፊቱን የማያዞርበትና ይኽንን መሰል አካሄድ ከማውገዝ የማይመለስበት አዝማሚያ እየታዬ ነው። ይኽንን ደግሞ እነሱም የሚያውቁትና የሚጨነርቁበት ጉዳይ እንደ-ሆነ ምንም ጥርጣሬ ሊኖር አይችልም። በዚኽም የተነሣ የኢሕአዴግ መሪዎች ይኽንን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አክራሪ ኃይሎች የቀሰቀሱት ብሔር/ብሔረሰብ ከብሔር/ብሔረሰብ፣ ሐይማኖት ከሐይማኖት የሚጋጩበት ትርምስ አድርገው በማቅረብ በውስጥ የሕዝቡን ሠፈር ለመከፋፈልና ለማዳከም፣ የሚያካሂዱት የአፈና ዘመቻ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲያገኝ ደግሞ መሞከራቸው የማይቀር ነው። ይኽንን የጥፋት ተልዕኮ ለማራመድ የወያኔ መሪዎችና በየብሔር/ብሔረሰቡ ያሉ ተባባሪዎቻቸው ቅስቀሣ የዚኽ ሕዝባዊ ትግል ማዕበል ዓላማ መንግሥታቸው ለብሔር/ብሔረሰቦች "ያረጋገጠውን" መብት ለመርገጥና "ዴሞክራሲያዊውን ፌደሬሽናችንን አፍርሶ በብሔር ጭቆና ላይ የተመሠረተ ሥርዓት እውን ለማድረግ ነው" የሚል እንደሚሆን ከእስካሁኑ ልማዳችን ያየነው እውነታ ነው። ይኽንን ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳቸውን ለማክሸፍ በተለይ በአገር-ውስጥ በይፋ የሚንቀሣቀሱት ኃይሎች በሚያካሂዱት ቅስቀሣ የሕዝባዊው ትግል ዓላማ እንዲያውም የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ የአገራችን ብሔረሰቦች በሙሉ የወያኔ መሪዎች የነፈጓቸውን መብት የማስመለስና የማረጋገጥ፣ ለብሔር/ብሔረሰቦች አርነትና በዴሞክራሲና በእኩልነት ላይ የተገነባ የአገር አንድነት ዓላማ እንደሆነ ለማሣየት ያልተቋረጠ ቅስቀሣ ማካሄድና በተጨባጭም እጅ-ለእጅ ተያይዘው መራመድና በሕዝባችን ፊት በአርኣያነት ቆመው መታየት ይጠበቅባቸዋል።

**መደምደሚያ፤**

ይኽ ፅሑፍ ስለ ጋራ ትግል አካሄዳችን ዛሬ በኅብረተሰባችን አስከፊ የሆነ ጨለምተኝነት ነግሷል፣ ትጥቅ-መፍታት አለ፣ ተቃዋሚው ጎራ በሕዝባችን ፊት ጨርሶ ተኣማኒነት አጥቷል ከሚለው ሃቅ ተነስቶ ይኽንን ለመወጣት ምን አጀንዳ ይዘን እንንቀሣቀስ? ይኽ ትግል ከተሣካልን ደግሞ እንደገና በሽብርና በኢሕአዴ መሪዎች የከፋፍለህ-ግዛ ስትራቴጂ መልሶ እንዳይፈታ ምን እናድርግ? በሚሉት ወሳኝ ጥያቄዎች ዙሪያ ውይይት ለመቀስቀስ የተሰናዳ ነው። በነዚኽ ጉዳዮች ላይ አንዳንድ አቅጣጫዎችን ለመጠቆም ቢሞክርም እነዚኽ በተግባር ስለሚተረጉሙበት ሁኔታ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎች ከማንሣት አልፎ አይሄድም።

አንድ በእርገጠኝነት ሊባል የሚችል ነገር ካለ መጀመሪያ ነገር የምንነድፈው ስትራቴጂም ሆነ አካሄድ እንዲሠምር በሁኔታው አስገዳጅነት በአገር-ውስጥ ባይቻል ግን ደግሞ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በአገር-ውስጥ ያሉ የተሰበጣጠሩ ኃይሎች ሰነዶችም ሆነ ሌሎች ግብአቶች የሚያቀርቡበት መንገድ ተፈልጎ ቢያንስ በውጭ-አገር ያለው ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ኃይል በሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ጥሪ አማካይነት በነዚኽ ነጥቦች ላይ በሠፊው ተወያይቶ የጋራ ትግል መርኅ ሰነድ (ማኒፌስቶ) ማፅደቅና በስምምነት የሚፀድቀውንም ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ታግሎ-አታጋይ የጋራ አካል የመፍጠሩ ጉዳይ ዛሬ-ነገ ሊባል የማይችል አጣዳፊ ተግባር መሆኑ ነው። የዚኽ ሁሉን-አቀፍ ስብስብ ኃላፊነት ቀጣዩን የዴሞክራሲ ሂደት ትግል በተመለከተ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ስለሚደረገው ትግል ስትራቴጂ አውጥቶ ያንን በተግባር በመተርጎም የሚወሰን አይሆንም።

በአገር-ውስጥም ቢሆን ቀጣይነት የሚኖረው ሕዝባዊ ትግል እምርታ ለመፍጠር በሕጋዊነት የሚንቀሣቀሱ የፖለቲካም ሆነ የሲቪል ማኅበረሰቡ ድርጅቶች ከፍ ብሎ በተጠቀሰው መልክ የእይታና የአደረጃጀት ለውጥ አድርገው እንዲንቀሣቀሱ እንዴትና ምን ማድረግ ይቻላል? በአገር-ቤት አንቀሣቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ግንባር-ቀደም ኃይሎችን አስተማማኝ የሆነ የኀቡዕ መዋቅር እንዲኖራቸው በምን ዘዴ ልንረዳ እንችላለን? በትጥቅ ትግል ለመሠማራት የሚፈልጉ አገር-ወዳድ ኃይሎች ይኽንን ሕዝባዊ ትግል "የመተካት" ሣይሆን የሱ የማይነጠል አካል ወይም አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉት እንዴት ነው? ይኽ ሁሉ ተቀነባብሮ ሁሉም በአንድ አቅጣጫ የሚገፋበት በጎ እምርታ ከተፈጠረ አይቀሬውን የወያኔ/ኢሕአዴግ ሽብር ለመቋቋም ገና ከወዲሁ ምን ተጨባጭ ዝግጅት ያስፈልጋል? ይኽ የጥፋት ኃይል ኀልውናውን ለማረጋገጥ ሲል የሚሠማራበትን የከፋናለህ-ግዛናአንዱን የሕዝብ ክፍል ከሌላው፣ ሐይማኖትን ከሐይማኖት የማናከስ ርኩስ ስትራቴጂ ሲቻል ቀድሞ ለማክሸፍ ካልሆነም ለመቋቋም ምን እርምጃዎች መውሰድ ይጠበቅብናል? እነዚኽ ሁሉ እጅግ ውስብስብ የሆኑ ጥያቄዎች የግል ድርጅትን ሣይሆን ሕዝብንና አገርን በሚያስቀድም መልክ በሚካሄዱ ውይይቶች መቋጠር ይኖርባቸዋል። ዛሬ ለሕዝብና ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ እንቆማለን የሚሉ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድርጅቶች አንገብጋቢና አጣዳፊ ተግባር እንዲኽ ዓይነቱን ውይይት እያበራቱ ወደ-አንድ የጋራ መፍትኄ የምንሄድበትን ጎዳና ማዘጋጀት ይመስለናል።

ከዚኽ በፊት "መሸጋሸግ፣ መሰባሰብ" በሚል ርዕስ ኅብረቱ አንድ መግለጫ አውጥቶ እንደ-ነበር ይታወሣል። በዚያ መግለጫ ላይ የተባለው የመጀመሪያው አካሄድ "መሸጋሸግ" የሚል ነውና እንዲኽ ዓይነቱ ጉባዔ "ተቃዋሚ" ነኝ የሚለው ሁሉ እስኪሰበሰብ መጠበቅ የግድ የለበትም። ጊዜ ለቀልባሾቹ እንጂ ለኛ እንደማይሠራና ትግላችን ከአደገኛ ዳተኝነትም ጋር መሆኑን ተገንዝበን፣ በሆነ-ባልሆነ ነገር ሊያራዝሙ የሚሞክሩ ኃይሎችን ወደ-ጎን ትቶ ፈቃደኛ ከሆኑ ወገኖች ጋር ይኽንን ጉባዔ ተግባራዊ ለማድረግ ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል። ያልነው አካሄድ የሕዝባዊ ኃይሎች "የመሰባሰብ" ሂደት ነውና በሕዝባችን ጎን የፀናን ወገኖች ቁጥራችን አነሰ የሚል ስጋት ሊኖረን አይገባም። ተሸጋሽገንና ተሰባስበን እናካሂድ የምንለው አሠላለፋችን የአገሩም፣ የትግሉም ባለቤት የሆኑትን ሚሊዮኖችን በግልፅ፣ ኢትዮጵያዊና ሕዝባዊ በሆነ አማራጭ ዙሪያ ታግሎ ለማታገል የሚሞክር አካሄድ እስከ-ሆነ ድረስ የጥራትና የቁርጠኝነት እንጂ የቁጥር ችግር እንደሌለበት ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

መጋቢት ፪ ሽህ ፱ ዓ/ም